በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1995 በጀት ዓመት
# የስድስት ወር የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥር 1995

## በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1995 በጀት ዓመት
# የስድስት ወር የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥር 1995

# ማ ው ጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


1. መግቢያ ---------- 1

2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ---------- 2
   2.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ---------- 2
   2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ---------- 5
   2.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ---------- 6
   2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ---------- 8

3. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ ---------- 12
   3.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ ---------- 12
   3.2 የመዛግብት አያያዝ ስታንደርድን በተመለከተ ---------- 13

4. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ ---------- 14
5. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት ---------- 15
6. ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ---------- 16
7. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ---------- 17
8. የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት ---------- 18
   ሀ. የሰው ኃይል አደረጃጀትን በተመለከተ ---------- 18
   ለ. የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ ---------- 19
9. የኦዲት አገልግሎት ---------- 20
10. የሕግ አገልግሎት ---------- 21
11. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ---------- 22

12. የሰው ኃይል ሁኔታ ---------- 22
13. የበጀት አጠቃቀም ---------- 24
    ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም ---------- 24
    ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም ---------- 25

14. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት ---------- 27
    ሀ. ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል ---------- 27
    ለ. ትራንስፖርትና ጥገናን በተመለከተ ---------- 28
    ሐ. ሕትመት ---------- 28

15. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ---------- 28

# የ1995 በጀት ዓመት የስድስት ወራት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ጠቀሜታ ያላቸው ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማጠናቀር፣ በመገምገምና በመተንተን ሪፖርት እያዘጋጀ ለመንግሥትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከአገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ዞን ድረስ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ ሪፖርት የሚዘጋጅላቸው ሲሆን፣ አለም አቀፋዊ መለኪያዎችንና ደረጃዎችን የጠበቁ እንዲሆኑም መ/ቤቱ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡፡

በመ/ቤቱ እየተዘጋጁ ለሚወጡት የስታቲስቲክስ መረጃዎች በየዓመቱ ከመንግሥት አስፈላጊ የሆነውን የበጀትና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ለመ/ቤቱ የሚደረግለት ሲሆን፣ የጥናቶቹም ጠቀሜታና ተቀባይነት በየጊዜው እያደገና እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በ1995 በጀት ዓመት የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ መ/ቤቱ ለመንግሥት አቅርቦና አስፈቅዶ በመንቀሣቀስ ላይ ሲሆን፣ ጥናቶቹ ባለፈው ዓመት የተጀመሩና የሪፖርት ዝግጅታቸው ወደ 1995 ዓ.ም የተሸጋገሩ እንዲሁም አዳዲስ ጥናቶችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ እነዚህም:-

### ሀ. በ1995 በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚካሄዱ ጥናቶች

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/፣
- የግብርና ግብአቶችና አሠራር ( Farm Management Practices ) ጥናት /በገጠር /፣
- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት/በተመረጡ ገበያዎች/፣
- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማ/፣
- አነስተኛና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማና በገጠር/፣
- የዕደ-ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በገጠርና በከተማ/፣
- የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት/በከተማ/፣
- መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት/በከተማ/፣ እና
- የኢንዴክሶች ዝግጅት ሥራ /በዋናው መ/ቤት/፣ ናቸው፡፡

ለ. <u>በ1995 የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ሥራዎች</u>

- የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የሚካሄድ የግብርና ናሙና ቆጠራ ማካሄድ፣ እና
- በአርሶ አደሩ አካባቢ በ1994 የተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የማተምና የማሰራጨት ተግባራት ናቸው::

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች ለማከናወን በባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1995 በጀት ዓመት ስድስት ወራት የተደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርቧል:: በተጨማሪም በሪፖርቱ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራት እንዲሁም በሩብ ዓመቱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ያጋጠሙ ችግሮችና የበላይ አካልን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

በ1995 በጀት ዓመት የሚጠኑ አብዛኛዎቹ ጥናቶች የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ፕሮጀክቶች ስር ለማካሄድ በዕቅድ የተያዙ ጥናቶችን በተመለከተ በዘርፉ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል::

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

#### 2.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

ሀ. <u>የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ</u>

- በ1995 ዓ.ም በመስከረም ወር በመስከ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ለተካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ መጠይቆች፣ የመረጃ ሰብሳቢዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሏል::

- ለዚሁ ጥናት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲት፣ ኮድና ቬሪፋይ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ኮድ ቡኮች ተዘጋጅተው በበቂ ኮፒ እንዲባዙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል::

- በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲካተቱ ለተደረጉ የአትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ከመስከ ለተሰበሰቡ መረጃዎች ቅንብር የሚያገለግል ቀመር (estimation procedures) እንዲሁም ወደ ኮምፒዩተር የገቡ መረጃዎችን በኮምፒዩተር ለማረም የሚያስችል computer edit specification አዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል።

- ለሰብል ምርት ትንበያ ጥናት አስፈላጊው የመረጃ ቅንብር በኮምፒውተር ከተከናወነ በኋላ በዞን፣ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁትን የጥናት ውጤቶች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ከሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ጋር አገናዝቦ የስታቲስቲክስ ሪፖርት ዝግጅቱን በማጠናቀቅና በበቂ ኮፒ እንዲባዛ በማድረግ ሪፖርቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

2.1.2 <u>የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤትን በተመለከተ</u>

ሀ. <u>የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የመኸር ወቅት ጊዜያዊ ሰብሎችን በተመለከተ በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና የምርት መጠን (Preliminary Results on Area, Production and Yield of Temporary Crops) የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1994 ዓ.ም ግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው በቋሚ ሰብሎች የተያዙ የመሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ቬሪፊኬሽንና የኤዲቲንግ ሥራ ተጠናቆ የቆጠራውን ውጤት የያዙ ሠንጠረዦች በመውጣት ላይ ይገኛሉ።

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት አካል የሆነው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቆጠራ ውጤት የመኸርና የበልግ እንዲሁም የገጠርና የከተማ የታረሰ የመሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በጊዜያዊና በቋሚ ሰብሎች መረጃ ተቀነባብሮ የወጣ ሲሆን፣ ሪፖርቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

- [illegible] (tabulation procedure) [illegible] tabulation plan specification [illegible]።

- [illegible]።

2.1.2 [illegible]

ሀ. [illegible]

- [illegible] (Preliminary Results on Area, Production and Yield of Temporary Crops) [illegible]።

- [illegible]።

- [illegible]።

ለ. <u>የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (Farm Management Practices) መረጃን በተመለከተ</u>

የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ አንዱ የሆነው የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ቀደም ብለው በተዘጋጁ የቆጠራውን ውጤት በሚያሳዩ ሠንጠረዦች ላይ ወጥተው የመረጃው አስተማማኝነትና መጣጣም እየተመረመረ ሲሆን፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ የመዠር፣ የበልግ፣ የገጠርና የከተማ መረጃ በሠንጠረዥ መልክ ወጥቶ ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የቤት እንስሳት፣ ዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃ የኢዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ለገጠሩ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። በመሆኑም የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የትግራይ፣ የአፋር የአማራና የኦሮሚያ ክልል መረጃዎች ተቀነባብረው ውጤቱ በመምሪያው ባለሙያዎች በመገምገም ላይ ይገኛል። የቀሪዎቹ ክልሎች የመረጃ ቅንብር፣ የከተማና የሰፋፊ/መካከለኛ እርሻዎች መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ማለትም በአፋር ክልል ሊደረግ ለታቀደው የቤት እንስሳት ቆጠራ የሚውሉ መጠይቆች መመሪያና የኢዲት ኮዲንግ መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

መ. <u>የመሬት አጠቃቀም (Land use) መረጃን በተመለከተ</u>

የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የመሬት አጠቃቀም መረጃ በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የውጤቱም ትክክለኛነትና አስተማማኝነት በባለሙያዎች እንዲገመገም ተደርጓል። በተጨማሪም ይህን መረጃ በተመለከተ በተሻሻለውና የቆጠራውን ውጤት ለማቅረብ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ የማዋሃድ ሥራ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መረጃ ላይ እየተካሄደ ሲሆን፣ የክልሉ መረጃ የገጠርና የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ተጠናቆ ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ነው።

ሠ. ሌሎች የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃዎችን በተመለከተ

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የምርት አጠቃቀም፣ የእርሻ መሣሪያዎችና ማከማቻዎች እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራዎች በመገባደድ ላይ ሲሆን፣ መረጃዎቹን ወደ ኮምፒዩተር የማስገባቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

- በ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃን ለእያንዳንዱ ክልል ሪፖርት በማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የቆጠራ ውጤትን በተለያዩ ርዕሶች በስምንት ምዕራፍ በመከፋፈል በመ/ቤቱ ባለሙያዎች የሪፖርት ዝግጅቱ በመከናወን ላይ ይገኛል::

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን በተመለከተ ኮድ የማዘጋጀቱ ሥራ ከሚቶዶሎጂ አገልግሎት ጋር በመሆን ከመጠናቀቁም በላይ የኮምፒዩተር ኤዲት ስፔስፊኬሽን ዶክመንት ተዘጋጅቶ ለመረጃ ማቀነባበር ተግባር እንዲውል ለሚመለከተው መምሪያ ተልኳል::

- በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ከሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች የተሰበሰበውን መረጃ ራሱን ችሎ በአንድ ስታቲስቲክስ ሪፖርት መልክ ለማዘጋጀት እንዲቻል የሪፖርቱ መንደርደሪያ ጽሑፍ ዝግጅትና ተዛማጅ ሥራዎች ተጀምረዋል::

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንደክሶችን ሥራ በተመለከተ

ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት

- ከመስከረም ወር 1994 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1994 ዓ.ም ድረስ ያሉ መረጃዎች የዳታ ኢንትሪና የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቆና ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሕትመት ተልኳል::

- የ1995 በጀት ዓመት የሚያገለግለው የዋጋ ጥናት መጠይቅ ታትሞ እንዲሰራጭ የተደረገ ሲሆን፣ መረጃውም ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል::

ለ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- እስከ ሰኔ 1994 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ቅንብሩ ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።
- የሐምሌና የነሐሴ 1994 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጀምሯል።

ሐ. <u>የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንደክስ ዝግጅት</u>

- <u>የ1993 ዓ.ም መሠረት የሚያደርገው የሸማቶች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>

– የ11 ክልሎች/ መስተዳድሮች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀው የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዞች ስሌት ከሚያዚያ ወር 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ላሉት ወራቶች ተከናውኖና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

– ከሐምሌ ወር 1994 ዓ.ም እስከ ጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ያለው የ11 ክልሎች/ መስተዳድሮች እና በአገር አቀፍ ደረጃ ጠቋሚ አሃዞች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል። እንዲሁም የኅዳር ወር 1995 ዓ.ም መረጃ ለሕትመት በመዘጋጀት ላይ ነው።

– የአዲስ አበባ ከተማ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ ታህሣሥ ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ያለው ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

## 2.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

### 2.3.1 <u>የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራሽን ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

- በመጋቢት ወር 1994 ዓ.ም የተሰበሰበው የ1993 ዓ.ም የዘርፉ ጥናት መረጃ የኢዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የሠንጠረዥ ቅንብር ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።
- በ1995 ዓ.ም ሊካሄድ ለታቀደው የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት የሥራ ክንውኑ፣ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የመጠይቆቹ ክለሣ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

ለ. <u>የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

በ1995 ዓ.ም የተካሄደው የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በገጠርና በከተማ/ የመጠይቅና የአሞላል መመሪያ ክለሣ ሥራ ተከናውኖና ለመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቶ የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል።

ሐ. <u>የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በተመለከተ</u>

የዘርፉ የ1993 ጥናት መረጃ ተሰብስቦ፣ ተጠናቅሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

መ. <u>የጎጆ/ዕደጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

በገጠር ለተካሄደው የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ክለሣ ሥራ ተከናውኖና ለመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቶ የመረጃ መሰብሰብ ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል።

ሠ. <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንደክስ ሥራን በተመለከተ</u>

የ1993 ዓ.ም የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የኢንደክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ረ. <u>የውጭ ንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ</u>

- የ1993/94 ዓ.ም የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተሰባስበዋል።
- እ.ኤ.አ የ2000 እና የ2001 የውጭ ንግድ መረጃ ሙሉ በሙሉ ተሰብስቦና የመረጃ ቅንብር ሥራው ተከናውኖና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

ሰ. <u>መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ (Informal Sector/ ጥናትን በተመለከተ</u>

በ1995 በጀት ዓመት በመካሄድ ላይ ላለው መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ /Informal Sector/ ጥናት የሥራ ክንውኗ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ መጠይቅና የአሞላል መመሪያ የከለሣ ሥራ ተከናውኖ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል።

ሸ. <u>የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናትን በተመለከተ</u>

በ1995 ዓ.ም በመካሄድ ላይ ላለው የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት የሥራ ክንውን የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ፍላጎት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ መጠይቅና የአሞላል መመሪያ የከለሣ ሥራ ተከናውኗል። እንዲሁም ይህንኑ ጥናት ለማካሄድ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተጀምሯል።

2.4 <u>የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

2.4.1 <u>የትምህርት፣ ባህልና ስፖርት፣ ሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ</u>

ሀ. <u>የባሕልና ስፖርት ስታቲስቲክስ</u>

የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናከር እንዲረዳ ሙያዊ እገዛ እንዲደረግለት በጠየቀው መሠረት አስፈላጊው ትብብርና እገዛ ተደርጓል።

ለ. <u>የትምህርት ስታቲስቲክስ</u>

የ1994 ዓ.ም የትምህርት መረጃዎችን ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተሰብስበው ሠንጠረዦቹ በመሠራት ላይ ይገኛሉ።

ሐ. <u>የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ</u>

- የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ በተመለከተ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል የመረጃ ምንጭ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር አስፈላጊው ውይይት የተደረገ ሲሆን፣

መሰብሰብ የሚገባቸው መረጃዎችና የመረጃ አሰባሰብ ስልቱን በሚመለከት ሪፖርት እየተዘጋጀ ይገኛል።

- ወጣቱን በሚመለከት የፖሊሲ ፍሬም ወርክ ለማዘጋጀት በአገር አቀፍ ደረጃ በተቋቋመው ግብረ-ኃይል መ/ቤት በአባልነት እየሰራ ይገኛል።

መ. <u>የጤናና የአመጋገብ ስታቲስቲክስ</u>

- የኤች አይቪ /ኤድስን ለመቆጣጠርና ለመገምገም በተዘጋጀው ዶክመንት ላይ ለመወያየት በተካሄደ አውደ ጥናት መ/ቤቱ የተሣተፈ ሲሆን፣ በግብረ ኃይል አባልነትም ተመርጦ በመሥራት ላይ ይገኛል።

2.4.2 <u>የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ</u>

- በ1993 ዓ.ም ተካሂዶ የነበረው የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት " Report on Child Labour Survey 2001" ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ የታተመ ሲሆን፣ ሪፖርቱን ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት እንዲቻል የሥራው ተባባሪ /partner/ ለሆነው ለሠራተኛና ለማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለዓለም ሥራ ድርጅት /ILO/ ኮፒ ተልኮ ሪፖርቱ እንዲሰራጭ ከስምምነት ላይ ተደርሷል።

- ይህንኑ ጥናት በሴሚናር መልክ ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅ እንዲቻል በሴሚናሩ የሚቀርቡ የመግለጫዎችና የግራፎች ረቂቅ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ሌሎችም በዶክመንት መልክ እንዲቀመጡ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

- በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማቀነባበርና (Employment/Unemployment/ በተጨማሪ ሪፖርት ለማዘጋጀት እንዲቻል Outline እና የሠንጠረዥ ረቂቅ /Dummy table/ ተዘጋጅቷል።

2.4.3 <u>ተከታታይ የሰው ኃይል ጥናትን በተመለከተ (Current Employment Survey)</u>

ተከታታይ የሆነ የሥራ ሥምሪት መረጃን ለማመንጨት በዚህ ዘርፍ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የመረጃ ፍላጎትና ክፍተቱን ለማጥበብ ለሚደረገው ጥናት

ዝግጅት እየተካሄደ ሲሆን፤ ለጥናቱ እንዲረዳ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ በጥናቱ ሊሰበሰቡ የሚችሉ መረጃዎችን... ወዘተ የሚገልጽ ጽሑፍ /Proposal/ እየተዘጋጀ ይገኛል። ይህንኑ ጥናት በከተማ ለመጀመር ዕቅድ ተይዟል።

### 2.4.4 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር "Functioning of Statistics and Planning in Federal Institutions" የሚል ጥናት ለማካሄድ መ/ቤቱ ተሳትፎ አድርጓል። እንዲሁም Labour Market Information Net Working ን በተመለከተ መ/ቤቱ በአገር አቀፍ የቴክኒካል ኮሚቴ ውስጥ እየተሣተፈ ይገኛል።

- የተለያዩ መ/ቤቶች ለሚጠይቁት መረጃዎችና የሙያ ድጋፎች እንደ አስፈላጊነቱ እገዛ ተደርጓል።

## 3. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅት፣ መዛግብት አያያዝና ስታንዳርድስ

በዚህ ክፍል በየዓመቱ ለሚካሄዱ የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች እንዲሁም ለጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ በክፍሉ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውኗል።

### 3.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ

- ለ1995 የሰብል ትንበያ ጥናት የሚያገለግል ሰርቬይ ዶክመንት ከ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ውስጥ የአንደገና Sub sample በመውሰድ የናሙና ምርጫ ተካሂዶና ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም ከነዚህ የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ውስጥ የአምራች ዋጋ ጥናት የሚካሄድባቸው ተለይተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።
- ለ1995 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናት እና የገጠር የጎጆ /የዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናቶች አስፈላጊው የሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።
- የ1995 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ናሙና ጥናት ማባዣ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን፣ ውጤቱንም ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ለመገምገም ተችሏል።
- በ1995 ለሚካሄደው የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናት የሣምፕሊንግ ፍሬም ወቅታዊ /Update/ የማድረግ ሥራ ለገጠሩ የናሙና ምርጫ ተካሂዶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።
- በ1995 ዓ.ም በመካሄድ ላይ ላሉት የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት (በገጠርና በከተማ) እንዲሁም የከተማ የጎጆ/የዕደ- ጥበብ ኢንዱስትሪ ናሙና ጥናቶች የሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን፣ ለነዚሁ ጥናቶች የናሙና ምርጫ ተካሂዶ አስፈላጊው ሥልጠና ለባለሙያዎች ተሰጥቷል።

- የ1994 ዓ.ም መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍን ጥናትና እንደዚሁም የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናትን በተመለከተ አስፈላጊው የሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ ተዘጋጅቶና የናሙና ምርጫ ተካሂዶ ዝርዝሩ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል።
- የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው የከተማ ግብርና ናሙና ቆጠራ የቀረ ክልሎች የማባዣ ሥራ ዝግጅትን ለመስራት አስፈላጊ ግብአቶችን አገልግሎቱ በመሰብሰብ ላይ ነው።
- በተመሣሣይ የሰፋፊ መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ኮድ ቡክ የአራት ክልሎች ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።
- የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት (Welfare Monitoring) አስመልክቶ በአዲስ የአሠራር ዘዴ Core welfare Indicator Questionnaire (CWIQ) ጥናቱን ለማካሄድ በክፍሉ ባለሙያዎች አስፈላጊው ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል።
- የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል ለሆነው የመኸር ወቅት መረጃ ለሁሉም ክልሎች የማባዣ /Raising Factor/ እና ውጤቱን የመገምገም ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከተው መምሪያ ተሰጥቷል።
- ሰርቬይ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ለሌሎች መንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ሙያዊ እገዛ ተደርጓል።

<u>የመዛግብት አያያዝና ስታንዳርድን በተመለከተ</u>

- በመ/ቤቱ ውስጥ የሚካሄዱ ጥናቶች፣ መጠይቆችንና ቅጾችን በመመርመር በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ ለአንድ ጥያቄ የተለያዩ አማራጮችና ኮዶች የተሰጠባቸውን ጥያቄዎችና ጥናቶች በመለየት ልዩነቱን ለማስታረቅ እንዲቻል ዝርዝሩ ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት ቀርቧል።
- በጎጆ /ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት ውስጥ የሚገኙ ጽንሰ ሃሣቦችን በተመለከተ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር የሚጠቀሙባቸው ጽንሰ ሃሣቦች ተዘጋጅተው ለአስተያየት ቀርቧል።

- የመ/ቤቱ ኢንዱስትሪ መምሪያ በአካሄዳቸው በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ ለስታቲስቲክስ ሥራ የሚያገለግሉ የፅንሰ ሃሣቦች፣ ትርጉሞችና የአጠያየቅ ስልቶች ሥራ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑና ማንዋሉቹ ማሟላት ያለባቸው ነጥቦች ተዘጋጅተው ለአስተያየት ቀርበዋል።

- ለስታቲስቲክስ ሥራ የሚያገለግሉ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች /ሥራ ዘርፎች ምደባ፣ አጠቃላይ የሙያ (Occupation) ምደባና ደረጃቸውን የጠበቁ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚረዱ የሪፖርት አፃፃፍ ስታንዳርድ ተዘጋጅተው ለአስተያየት ቀርበዋል።

- ከተለያዩ የውጭ መ/ቤቶች በቀረበው የካርታ ጥያቄ መሠረት የሚፈልጓቸውን ቦታዎች የያዙ /የሚጠቁሙ/ ካርታዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል።

## 4. የ1994 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ሁኔታዎች የሚገልጹ መረጃዎችን የሚያካትተው የ1994 ዓ.ም ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መ/ቤቶች እንዲሁም ድርጅቶች በአብዛኛው ተሰብስቧል። ይህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ እነዚህም

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የውጭ ንግድ መረጃዎች፣
- ዓመታዊ የሀገር ሃብት መረጃዎች
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የመድህን /ኢንሹራንስ/መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣

- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የስፖርትና ሲኒማ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

<u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

- ከተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ግለሰብ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በ1995 ዓ.ም ለሚካሄዱ ጥናቶች የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በጥናቱ ላይ ለሚሣተፉና ለሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች እንዲሁም የጽ/ቤት አስተባባሪዎችና ስታቲስቲሽያኖችን በመስልጠኛ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ በመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡
- ለመ/ቤቱ የ1994 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚውሉና ከሌሎች መ/ቤቶች መሰብሰብ ያለባቸው መረጃዎች እንዲሰበሰቡ አስፈላጊው ዝግጅት ተካሂዶ፤ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፤ በሠንጠረዥ መልክ ተዘጋጅተው ወደሚመለከታቸው ክፍል ተላልፈዋል፡፡
- መ/ቤቱ ከUSAID በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በአማራ ብሔራዊ ክልል ተደጋጋሚ ድርቅ በሚከሰትባቸው ሦስት ዞኖች ለተመረጡ ሦስት ወረዳዎች ማለትም በደቡብ ጎንደር ላይ ጋይንት ወረዳ፣ በሰሜን ወሎ ጉባላፍቶ ወረዳና በዋግኸምራ ዞን በሰቆጣ ወረዳ ለሚካሄድ ጥናት በናሙና በተመረጡ 75 የቆጠራ ቦታዎች መረጃ ሰብሳቢዎችን በመመልመልና በማሰልጠን አስፈላጊ መረጃ ተሰብስቦ ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡
- የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናትን /Welfare Monitoring Survey/ አስመልክቶ በአዲስ የአጠናን ዘዴ በአገራችን ለመጀመር እንዲቻል ከዚህ በፊት ጥናቱን ካካሄዱ አገሮች ልምድ ለመቅሰምና የሙከራ መነሻ የሆነ መረጃ ለማግኘት ባለሙያዎች ጋናና ማላዊ ለአንድ ሳምንት ጥናታዊ ጉብኝት አድርገው ተመልሰዋል፡፡

- ከFAO እና መሰል ድርጅቶች ለሚቀርብ የመረጃ ጥያቄዎች አስፈላጊውን መረጃና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

## የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት

- ማሻሻያ ጽ/ቤቱን በመ/ቤቱ ውስጥ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ በማደራጀት አስፈላጊውንና የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

- የ1995 መጀመሪያ ዙር የሥራ ዕቅዶችና መለኪያዎች በወቅቱ እንዲዘጋጁ፣ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱም በመረጃ ላይ ተመስርቶ እንዲሞላና የ1995 ሁለተኛው ዙር የሥራ ዕቅዶችና መለኪያዎች ዝግጅት በወቅቱ እንዲደርሱ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

- ስለአዲሱ የሥራ አፈጻጸም ሁኔታ ግምገማ ለማካሄድ ከዋናው መ/ቤት ከሚገኙ ቋሚ ሠራተኞች ውስጥ 10 በመቶ ናሙና በመምረጥ ግምገማው ተካሂዶ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

- ወደ መ/ቤቱ ለሚመጡ የውጭ ተገልጋዮች የሚፈልጓቸውን የሥራ ክፍሎች በቀላሉ ሊያገኙዋቸው እንዲችሉ የሚያግዝ የመረጃ መስጫ ክፍልና ሠራተኛ ተመድቧል፡፡ እንዲሁም የቢሮዎችን አቀማመጥ፣ የሕንፃዎችንና የሥራ ክፍሎችን አድራሻ የሚገልጹ ሰሌዳዎች ተሰርተው በሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን፣ በሕንፃዎችና በቢሮዎች ላይ መለያ ቁጥርና የሥራ ኃላፊነት ደረጃ በቢሮዎቹ በር ላይ እንዲለጠፉ ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን ዓላማና ተልዕኮ የሚገልጹ መልዕክቶች በቋሚ ሠሌዳዎች ላይ ተሰርተው ለዕይታ አመች በሆኑ ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

- በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙና ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጭ ለሆኑ የመ/ቤቱ ቋሚ ሠራተኞች የደረት ባጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

- የተገልጋዮች ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ክፍል፣ የአቤቱታና የቅሬታ መቀበያና መልስ መስጫ ቅጾች ተዘጋጅተውና ተባዝተው በዋናው መ/ቤትና

በቅ/ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች እንዲደርሷቸውና በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- መ/ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን በውጭ ተገልጋዮች መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ባለጉዳዮች በሚሰጧቸው አገልግሎቶች ቅር ቢሰኙ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የሚገልጹ ጽሑፎች በቋሚ ሠሌዳዎች ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል።
- የመ/ቤቱን ድርጅታዊ ብቃት ለመገምገም አንድ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ያዘጋጀውን መነሻ መጠይቅ ለመ/ቤቱ በሚሆን ይዘት እያዘጋጀ ይገኛል።
- የመ/ቤቱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍልና የሥነ-ምግባር መኮንን ተመድቦ ሥራው የተጀመረ ሲሆን፣ ሙስና ሊከሰትባቸው የሚችሉ የአገልግሎት ክፍሎች አሠራር ተፈትሿል።
- መ/ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ የተገልጋዮችን አስተያየት ለመሰብሰብ እንዲቻል ተገልጋዮች በናሙና ተመርጠው ስለመ/ቤቱ አገልግሎት አሠጣጥ አስተያየት ተሰብስቦ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

## <u>የማስታወቂያ ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት</u>

- በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 84 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት፣ 699 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ውጤት ሪፖርቶች፣ 133 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ሪፖርቶች፣ 1,270 የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ሪፖርቶች፣ 867 የዋጋ ጥናት ሪፖርቶችና 386 የኢንዱስትሪ ጥናት ሪፖርቶች በጠቅላላው 3,437 የጥናት ሪፖርቶች በነፃ ተሠራጭተዋል። እንዲሁም 181 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች፣ 342 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ውጤት ሪፖርቶች፣ 243 የዋጋ ጥናት ሪፖርቶችና 157 የኢንዱስትሪ ጥናት ሪፖርቶች በጠቅላላው 1,456 ሪፖርቶች ደግሞ በብር 39,747.65 ሽያጭ ተፈጽሟል። በመሆኑም በጠቅላላው ባለፉት ስድስት ወራት የ4,893 የጥናት ሪፖርቶች ስርጭት ተከናውኗል።

- ለመጀመሪያ ጊዜ ለመ/ቤቱ ልሣን ይሆናል ተብሎ የታሰበው "ዜና ማስባ" ተዘጋጅቶና ለመ/ቤቱ ኢዲቶሪያል ኮሚቴ ቀርቦ ፀድቋል።

- የመ/ቤቱ ቤተመጻሕፍት ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች፣ ከውጭና ከሃገር ውስጥ ለሚመጡ በጥናትና ምርምር ሥራ ላይ ለሚሣተፉ ግለሰቦችና መረጃ ፈላጊዎች ያለማቋረጥ የንባብና የመጽሐፍ ውሰት አገልግሎት ተሰጥቷል።

- እንዲሁም ወደፊት መ/ቤቱ ለሚያዘጋጃቸውና ለሚያሣትማቸው የውስጥ የዜና መጽሔቶች፣ ብሮሹሮች፣ ቡለቲኖች... ወዘተ የማማከር ሥራዎች ላይ የሚሣተፈው የኢዲቶሪያል ኮሚቴ መተዳደሪያ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለማኔጅመንት ቀርቧል።

- የመ/ቤቱን ቤተመፃሕፍት ለውስጥና ለውጭ ተጠቃሚዎች የተሻለ ለማድረግ ተጨማሪ መፃሕፍት ግዢ ለማካሄድ አስፈላጊው ፋርማሊቲ እየተጠናቀቀ ይገኛል።

- በመ/ቤቱ አማካይነት የሚካሄዱ ጥናቶችና የወጡ የጥናት ሪፖርቶችን እንዲሁም በየጊዜው ስለሚሰጡ የጥናት ሥልጠናዎች ይዘት ሕብረተሰቡ እንዲያውቃቸው ለማድረግ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል።

- ከአገር ውስጥና ከውጭ በማንባር ለሚመጡና በደብዳቤ ለሚቀርቡ ልዩ ልዩ የመረጃ ጥያቄዎች ተገቢው ምላሽ ተሰጥቷል።

## የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት

### ሀ. የሰው ኃይል አደረጃጀትን በተመለከተ

- በመላው አገሪቱ በሚገኙ 25 ቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናው መ/ቤት ሕግን የተመለከቱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የተመደበው አንድ የሕግ ባለሙያ በመሆኑ በየጊዜው የሚነሱ ሕግ-ነክ ጉዳዮችን ተከታትሎ ለማስፈጸም አስቸጋሪ ሆኗል። በመሆኑም በ1994 ዓ.ም መ/ቤቱ ያለበትን ችግር ለማቃለል እንዲችል ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሦስት የነገረፈጅ መደቦች እንዲፈቀዱለት በጠየቀው መሠረት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በኮሚሽኑ ተፈቅዷል።

- በ1995 ዓ.ም ለሚካሄዱ የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናት በከተማና ለአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት በከተማና በገጠር የአሰልጣኞች ሥልጠና ከኅዳር 5 ቀን 1995 እስከ ኅዳር 11 ቀን 1995 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የተሰጠ ሲሆን፣ ለመስክ ሠራተኞች ደግሞ ከኅዳር 16 ቀን 1995 እስከ ኅዳር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በቅ/ጽ/ቤቶች ተሰጥቷል። እንደዚሁም በዚሁ ዓመት ለሚካሄዱት መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍና የአከፋፋይ ንግድ ድርጅት ጥናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ከታህሣሥ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 23 ቀን 1995 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የተሰጠ ሲሆን፣ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ከታህሣስ 28 1995 ዓ.ም ጀምሮ በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ለተከታታይ 13 ቀናት ይካሄዳል።

- ለመ/ቤቱ ሠራተኞች አዲስ የወጣውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በገጠር ልማት፣ በአቅም ግምባታና በዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ተወያይቶ አንድ አገራዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። በዚሁም መሠረት የዋናው መ/ቤት ሠራተኞችን በሁለት በመከፈል ሥልጠናና ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ለ22ቱ ቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች በ8 የሥልጠና ማዕከላት ከላይ በተጠቀሱት ርዕሶች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል።

## 9. የኦዲት አገልግሎት

- መ/ቤቱ በ1994 ዓ.ም ለግብርና ናሙና ቆጠራ የተፈቀደለት ከፍተኛ በጀት በነባርና አዲስ በተከፈቱ በጠቅላላው 47 ቅ/ጽ/ቤቶች ለሥራ በመሳኩ በአንዴና በሚፈለገው ጊዜ ተወራርዶ መጠናቀቅ አልቻለም። በመሆኑም፡-

  - አገልግሎቱ በኦዲት ደንብና መመሪያ መሠረት ሂሣቡን መርምሮና አጣርቶ እንዲወራረድ አድርጓል።

  - ከነዚህ ጽ/ቤቶች ሊወራረዱ ከሚመጡ ሰነዶች መካከል የነዳጅ ወጪዎችን ለመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የዋለ መሆኑና በኪሎሜትር የተጠቀሙበት መጠን ከኪሎ ሜትር ካርድ ጋር በማገናዘብና በመቆጣጠር ደረሰኞች እንዲወራረዱ አድርጓል።

- የጎንደርና የአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል አግኝተው ትምህርት ቤት በመግባታቸው፣ እንዲሁም የጂጂጋ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ወደዋናው መ/ቤት በመምጣታቸው ሲያንቀሳቅሱት የነበረውን የመንግስት ገንዘብ በመመርመር በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቱ ኦዲተሮች አማካይነት ርክክብ እንዲያደርጉ ተደርጓል።

- የዋናው መ/ቤት ገንዘብ ያዥ ርክክብ ለመፈፀም እንዲቻል የገንዘብና የንብረት ዝርዝር የሚገባ ምርመራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- በ1994 ዓ.ም ለተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በመንግሥትና በዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የተገዙ በርካታ የመስክ መገልገያ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደዋናው መ/ቤት እንዲመለሱ ተደርጓል። ይህ ንብረት በየዓመቱ ለሚካሄዱ ጥናቶችና ለተመሣሣይ ቆጠራ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ከ47 ቅ/ጽ/ቤቶች የመጣውንና መጀመሪያ የተላከበትን መረጃ ለማገናዘብ የንብረት ኦዲት ምርመራ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል።

- የዋናው መ/ቤት ንብረት ክፍል በ1994 ዓ.ም ያካሄደውን የንብረት እንቅስቃሴ ገቢና ወጪ እንዲሁም በክምችት የሚገኝ የመ/ቤቱን ንብረት የ1995 ስድስት ወራት ምርመራ አካሂዷል።

- የመ/ቤቱን የመጽሔት ሽያጭ ክፍል ያከናወነውን የነገና የሽያጭ የጥናት ሪፖርት ስርጭት ንብረትና ገንዘብ ምርመራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

## ሕግ አገልግሎት

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩት ጊዜ የመንግሥትን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ በመ/ቤቱ በተሰጣቸው የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት በጉድለት ከሚታየው ብር 19.503.52 ውስጥ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ብር 9.871.82 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

- በመ/ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ መ/ቤቱ የሚፈልግባቸውን በጠቅላላ ብር 74.951.26 ገቢ እንዲያደርጉ ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርቦ ውሣኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በሰዎች ላይ ላደረሱት ጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው በጠቅላላው ብር 404,840.20 በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል አቅርበው እየታየላቸው ይገኛል::

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሚቀርብባቸው ከባድ የዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት ሦስት ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ መ/ቤቱ ወስኖባቸው ውሣኔውን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያፀደቀው ሲሆን፣ ሌላ አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስ ተደርጓል:: እንዲሁም የአንድ ሠራተኛ ክስ በወረዳ ፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛል::

## 11 ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1995 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መረሃ-ግብሩ መሠረት የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል አስተላልፏል::

- የመ/ቤቱን ወርሃዊ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል አስተላልፏል::

- ከዚህ ቀደም ተዘጋጅቶ የነበረውን የመ/ቤቱን የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ጥናት ቅድም ተከተል ፕሮግራም ከሚመለከታቸው መምሪያዎች ጋር በመሆን የማሻሻል ሥራ አከናውኖ፣ ፕሮግራሙ እንዲፀድቅና ሥራ ላይ እንዲውል የበላይ አካልን ውሣኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

## 12. የሰው ኃይል ሁኔታ

በ1995 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,513 ቋሚና 2,213 የኮንትራት በጠቅላላው 3,726 ሠራተኞች ነበሩ:: ከነዚህ ቋሚ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ውስጥ 77 ሠራተኞች አዲስ ወደ ተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተዛወሩ፣ 20 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 17 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንዲሁም 8 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ የ32 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል::

እንደዚሁም በበጀት ዓመቱ ከነበሩ የኮንትራት ሠራተኞች ውስጥ 1,846 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 51 የዳታ ኢንትሪና የኤዲቲንግ ሠራተኞች፣ 68 የአስተዳደርና 118 ሾፌሮች

በጠቅላላው 2,083 የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ተፈፅሟል። በሌላ በኩል ደግሞ 3,481 ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ ተደርጓል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 2,238 ሲሆን፣ ከእነዚህ ሠራተኞች ውስጥ 1,423 ቋሚና 815 ደግሞ የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት መጨረሻ ላይ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,513 | 2,213 | 3,726 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 32 | 2,083 | 2,115 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (8) | - | (8) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (20) | (3,481) | (3,501) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (17) | - | (17) |
| 6 | ወደ ሌላ መ/ቤት የተዛወሩ | (77) | - | (77) |
| | ድምር | 1,423 | 815 | 2,238 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ወይም በሥራ መደብ ሲተነተን 103 ፕሮፌሽናል፣ 890 መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችና እንዲሁም 430 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። እነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,103 ወንዶች /77.5 በመቶኛ/ ሲሆን 320 ደግሞ ሴቶች /22.5 በመቶ/ ናቸው።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት መጨረሻ ላይ ያሉት ጠቅላላ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 3 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 89 | 788 | 226 | 1,103 | 20 | 341 | 165 | 526 | 1,629 |
| ሴት | 14 | 102 | 204 | 320 | 2 | 270 | 17 | 289 | 609 |
| ድምር | 103 | 890 | 430 | 1,423 | 22 | 611 | 182 | 815 | 2,238 |

## 13. የበጀት አጠቃቀም

ለ1995 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት የመደበኛና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 48,479,100 የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቪይ ፕሮግራም 19,688,300 ብር ለግብርና ናሙና ቆጠራ ተጣይ ስራዎች 14,138,400 ብር በጠቅላላው ለሁለቱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ብር 33,826,700 (69.8 በመቶ) የካፒታል በጀትና ብር 14,642,400 (30.2 በመቶ) ለመደበኛ በጀት የሚውል ነው፡፡

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በበጀት ዓመቱ ለመደበኛ ሥራዎች የተመደበውን ብር 14,652,400 በሦስት ዋና ዋና የወጪ አርዕስቶች በመከፋፈል ሥራ ላይ ለማዋል የታቀደ ሲሆን፣ ይኸውም

- ለደመወዝ---------------------------------------------------------ብር 12,826,100
- ለውሎ አበል---------------------------------------------------ብር 48,000
- ለሥራ ማስኬጃ-------------------------------------------------ብር 1,768,300 የሚውል ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ የመደበኛ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 6,010,727 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 5,811,011 ነው፡፡ አፈጻጸሙም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 39.7 በመቶ ሲሆን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ የገባው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 96.0 በመቶ ነው፡፡ ዝርዝሩም በሠንጠረዥ 4 ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የመደበኛ በጀት አፈፃፀም

| በጀት አጠቃቀም | ለ1995 በጀት ዓመት የተፈቀደ | በበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነው ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| ደመወዝ | 12,836,100 | 5,596,676 | 5,596,676 | - |
| ውሎ አበል | 48,000 | 6,401 | 5,874 | 527 |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,768,300 | 407,650 | 208,461 | 199,189 |
| ድምር | 14,652,400 | 6,010,727 | 581,011 | 199,716 |

ለ. <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

በ1995 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች በካፒታል በጀት ብር 33,826,700 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ ይኸውም ብር 19,688,300 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚውል ሲሆን፣ ቀሪው ብር 14,138,400 ደግሞ በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአርሶ አደሩ አካባቢ የተሰበሰበውን መረጃ ለማቀነባበርና ለሪፖርት ዝግጅትና እንዲሁም በ1995 ዓ.ም በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለሚካሄደው የግብርና ቆጠራ ማስፈጸሚያ የሚውል ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ለሁለቱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ በጠቅላላው ብር 14,802,765 ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 13,123,879 እንዲሁም ለግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች ደግሞ ብር 1,678,886 ወጪ ሆኗል። ዝርዝሩም በሠንጠረዥ 5 ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 5

## የ1995 ዓ.ም የስድስት ወራት የካፒታል በጀት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | የበጀት አጠቃቀም | የበጀት ኮድ | ለ1995 ዓ.ም የተፈቀደ በጀት | በስድስት ወራት ውስጥ ተጠይቆ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት /04 እና 05/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| 1. | <u>ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም</u> | | 19,688,300 | 9,753,414 | 13,120,880 | (3,367,466) |
| 1.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 7,333,800 | 3,560,814 | 3,907,479 | (346,665) |
| 1.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 2,939,700 | 1,185,000 | 1,102,923 | 82,077 |
| 1.3 | ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርትና..ወዘተ | 6230 | 6,076,000 | 4,115,400 | 6,192,944 | (2,077,544) |
| 1.4 | ለዕድሣትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 1,908,000 | 695,400 | 1,474,870 | (779,470) |
| 1.5 | በውል ለሚፈፀሙ አገልግሎቶች | 6251 | 1,280,800 | 196,800 | 432,964 | (236,164) |
| 1.6 | ለአገር ውስጥ ሥልጠና | 6271 | 150,000 | - | 9,700 | (9,700) |
| 2. | <u>የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች</u> | | 14,138,400 | 3,326,490 | 1,678,886 | 1,647,604 |
| 2.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 9,566,700 | 1,201,290 | 1,633,146 | (431,856) |
| 2.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 427,400 | 369,400 | 19,500 | 349,900 |
| 2.3 | ለውሎ አበል፣ ትራንስፖርት… ወዘተ | 6230 | 2,838,300 | 1,635,800 | 26,240 | 1,609,560 |
| 2.4 | ለዕድሣትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 299,000 | 70,000 | - | 70,000 |
| 2.5 | በውል ለሚፈፀሙ አገልግሎቶች | 6251 | 1,007,000 | 50,000 | - | 50,000 |
| | **ድምር** | | 33,826,700 | 13,079,904 | 14,799,766 | 1,719,862 |

## 14. የአገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

### ሀ. የጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- መ/ቤቱ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ ውሣኔ ካገኙ 16 የመስክ ተሽከርካሪዎች ውስጥ 8ቱ በብር 405,000 የተሸጡ ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ  በሁለተኛው የጨረታ ማስታወቂያም በቂ ተወዳዳሪ ባለመገኘቱ የመኪናዎቹ ሽያጭ ለጊዜው እንዲቆም ተደርጓል::

- ለ1995 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የጽ/መሣሪያና የጽዳት ዕቃዎች ግዢ እንዲሁም የኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የህትመት ማሽንና የፎቶ ኮፒ ማሽን የጥገና ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ለተገኙበት የጨረታ ሁኔታ ግዥ ተፈፅሟል::

- የ1995 በጀት ዓመት የደንብ ልብስ ጨረታ ሂደቱን ጠብቆ የተከናወነ ሲሆን፣ ተጫራቾች ካቀረቧቸው ናሙናዎች ሸሚዝ፣ ካኪ ጨርቅ የውስጥ ልብስ ሲመረጡ ቀሪዎቹ በሠራተኛ ተወካዮች ባለመመረጣቸው ጨረታው እንደገና እንዲወጣ ተደርጓል::

- መ/ቤቱ ለተገለገለበት የስልክ፣ የመብራት፣ የውኃና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ በወቅቱ እንዲፈፀም፣ እንዲሁም የተለያዩ የቢሮ ውስጥ የጥገና ሥራዎች በየጊዜው በሚመለከታቸው ሠራተኞች እንዲጠገኑና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል::

- መ/ቤቱ ያለው የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ በርካታ በመሆኑ አንዳንድ በአጭር ጊዜና በተደጋጋሚ ብልሽት ለሚያጋጥማቸው የመኪና ዕቃዎች በመ/ቤቱ መካኒኮች ጥገና እንዲደረግላቸው ለማድረግ እንዲቻል በአዲስ አበባ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ግቢ የጋራዥ ጉድጓድ እንዲሰራ ተደርጎ ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተመሣሣይ የጋራዥ አገልግሎት የአሠራር ልምድ ለመቅሰም አንድ ኮሚቴ ተሰይሞ ጊዜያዊ የአሠራር መመሪያ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል::

- መ/ቤቱ ላለበት የዶክመንት ማከማቻ ጥበት አገልግሎት የሚውል መጠኑ 12.70ሜ x 23.20ሜ የሆነ መጋዘን አስገንብቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በመጋዘኑ የብረት መደርደሪያ ለመስራት በጨረታ ዲክስን አንግልና ችፕውድ ለመግዛት

በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም መ/ቤቱ ላለበት አጣዳፊ ችግር በተወሰነ ደረጃ አነስተኛ መጠን ያለው መደርደሪያ ተገዝቶ የጥናት መረጃ የያዙ ዶክመንቶችን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

ለ. <u>ትራንስፖርትና ጥገና ዋና ክፍል</u>

- የ1995 ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ለ25 መኪናዎች ተደርጓል፡፡

- በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ የሰርቪስና የመስክ ተሽከርካሪዎች ባለፉት ስድስት ወራት ብር 84,767 ወጪ በማድረግ ነዳጅ፣ ቅባትና እጥበት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ 173 መኪናዎች ቀላልና ከባድ ጥገና በብር 1,271,172 ተደርጎላቸዋል፡፡

- በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ 21 የመድን ሽፋን የነበራቸው ተሽከርካሪዎች በመድን ድርጅት እንዲጠገኑ ተደርጎ ወደ ሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ ሌሎች 6 መኪኖች በጋራዥ ይገኛሉ፡፡

ሐ. <u>የሕትመት ዋና ክፍል</u>

የመ/ቤቱ የሕትመት ዋና ክፍል ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ 6,254,820 ገጽ ያላቸው 102,318 የተለያዩ ዓይነት ጥራዞች አትሞ ለሚመለከተው ክፍል ያቀረበ ሲሆን፣ ከመምሪያዎችና አገልግሎቶች ለሚቀርቡለት የፎቶ ኮፒ አገልግሎቶች ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

## 15. <u>በዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች</u>

ሀ. መ/ቤቱ በየዓመቱ አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን ጥገና በማካሄድ ለረጅም ጊዜ እንዲሰሩ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም በበጀት ዓመቱ የኢንሹራንስ ሽፋን የሚያገኙት የመንግሥት ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከ10 ዓመት መብለጥ የለበትም የሚለው የመንግሥት አሠራር የመ/ቤቱን በርካታ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ከመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች 15 በመቶውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከተጠቀሰው ዓመት በላይ ለሆኑና

በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ጥቅም በመስጠት ላይ ያሉ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን የሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት መንግሥት ያወጣውን መመሪያ እንደገና መመልከት ወይም ሌላ አማራጭ መፍትሄ እንዲሰጠን እንጠይቃለን።

ለ. መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ ሪፖርቶችና ሌሎች የሕትመት ሥራዎችን የሚያካሂደው በራሱ ማተሚያ ቤት በመጠቀም ነው። ማተሚያ ቤቱ ከመንግሥትና ከረጂ ድርጅቶች ላለፉት ዓመታት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በርካታ የማተሚያ መሣሪያዎች፣ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የፎቶ ኮፒ መሣሪያዎች፣ የፎቶ መቅረጫዎች፣ የወረቀት መቁረጫዎችን መጠረዣ ማሽኖች እንዲኖሩት ተደርጓል። ሆኖም ከአገልግሎት ብዛትና ከዕድሜ መግፋት የተነሣ መሣሪያዎቹ ተደጋጋሚ ዕድሣትና ሰርቪስ የሚያስፈልጋቸው ሆነዋል። በመሆኑም የመሣሪያዎቹ ብቸኛ የአገር ውስጥ ወኪሎችና በመንግሥት የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱት የጥገና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መ/ቤቱ ለሚያቀርበው የሰርቪስ /የጥገና ጥያቄ የሚሰጡት መልስ ድርጅቶቹ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር አጥጋቢ አይደለም።

ይህ በመሆኑም መሣሪያዎቹን ለማስጠገን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ ቢያወጣም የሚቀርቡት ተወዳዳሪዎች መሣሪያዎቹን የማያውቋቸውና የመጠገንም ብቃት የሌላቸው ሲሆኑ፣ የመሣሪያዎቹ ብቸኛ አቅራቢ ድርጅቶች የሚባሉትም ዕቃዎቹን ከሸጡ /ከአቀረቡ/ በኋላ የተሟላ የጥገና አገልግሎት መስጠት እንደማይጠበቅባቸው በመገመት ለሚቀርብላቸው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ አይሰጡም። ስለዚህ የመ/ቤቱን ማተሚያ ቤት መሣሪያዎች ለማስጠገን እንዲቻል ከመንግሥት የአቅራቢዎች ዝርዝር ውጪ ያሉ ድርጅቶችን በመንግሥት የዕቃ ግዥ መመሪያ መሠረት ተከትሎ መ/ቤቱ ሊያስጠግን የሚችልበት ሁኔታ እንዲመቻች እንጠይቃለን።

ሐ. መ/ቤቱ ላለፉት ተከታታይ የበጀት ዓመታት ያለበትን የቢሮ ችግር/ዕጥረት በተደጋጋሚ ጊዜ ለበላይ አካል ማቅረቡ ይታወሣል። ሆኖም መ/ቤቱ ይህን ያለበትን ችግር ለመቅረፍ ረጅም ጊዜ የሚወስድበት በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ አማራጭ ሲጠብቀው የነበረው ከመ/ቤቱ በመንግሥት ፈቃድ ራሱን ችሎ የወጣውና የተደራጀው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የራሱን ቢሮ ያገኛል የሚለው ነበር። ቢሆንም ኮሚሽኑ አሁን ከያዘው የመ/ቤቱ ቢሮዎች ወጥቶ ወደሌላ ጽ/ቤት የሚገባበትን ጊዜ እያራዘመ በመሆኑ የመ/ቤቱ ቢሮ ችግር ሊቃለል አልቻለም። ስለዚህ ለመ/ቤቱ የአጭር

ጊዜ የቢሮ ችግር መፍትሄ ኮሚሽኑ ከያዛቸው ቢሮዎች ለቆ መውጣት ስለሆነ የበላይ አካል አንድ መፍትሄ እንዲሰጥበት እንጠይቃለን።

መ. አዲሱ የሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ተግባራዊ ከሆነ በርካታ ወራቶች አልፈዋል። ሆኖም በውስጡ ረጅም ጊዜና ጥናት የሚያስፈልጋቸው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል ደንብ እንዲወጣላቸው የሚጠብቁ የአዋጅ አንቀጾች መኖራቸው ለመ/ቤቱ አሠራር ችግር እየሆኑ መጥተዋል። እነዚህም በተጠባባቂነት ለሚመደቡ ሰራተኞች ለቦታው የሚከፈለውን ደመወዝ አለመከፈል፣ ልዩ ልዩ የኃላፊነት አበል አለመፈቀዱ፣ የሕክምና ሽፋን የሚያገኙበት አሠራርና የመሳሰሉት ጥቅማጥቅሞችን ሰራተኛው እንዲያገኝ ባለመፈቀዱ ምክንያት መንግስት ብዙ ገንዘብ አውጥቶና ደሥሩልኛል ብሎ ያስተማራቸው ሠራተኞች የተሻለ ክፍያ ፍለጋ ሥራቸውን እየለቀቁ ይገኛሉ። ስለዚህ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ አሠራር እስከሚወጣ ድረስ የመ/ቤቱን ባለሙያዎች በቦታቸው ለማቆየት መፍትሄ የሚገኝበት ሁኔታ እንዲመቻች እንጠይቃለን።